በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 213041

ቀን ሚያዝያ 26 2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ ወ/ሮ ወይንሸት ወርቁ ጅማ --ወኪል ወርቅነህ ነገዎ ቀረቡ

ተጠሪ፡ አቶ ፈይሳ ኃይሌ ሮቢ --ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 31939 በ9/7/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 32664 በ20/8/13ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 375407 በ25/9/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ17/12/13ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በስር የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት 2ኛ ከሳሽ ሆነው፤ አሁን ሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉት ፈቃዱ ስሜ(የስር 1ኛ ከሳሽ)፤ ብርሃኑ ኃይሌ(ስር 3ኛ ከሳሽ) ሆነው በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) እና አሁን ሰበር ክርክሩ ላይ በሌሉት ወ/ሮ ደሚቱ ሮቢ(ስር 1ኛ ተከሳሽ) ላይ ባቀረቡት ክስ ለስር 1ኛ ተከሳሽ አያታችን ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ አክስቷ ሲሆኑ፤ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ደግሞ የአያታችን የልጅ ልጅ ሲሆን አያታችን ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ በ24/1/10ዓ.ም ሞታለች፡፡ ሟች አያታችን ያላት ልጆች 4 ይኸውም የስር 1ኛ ተከሳሽ አባት፤ ኃይሌ ሮቢ፤ የስር 1ኛ ከሳሽ አባት ስሜ መርጋ፤ የአመልካች(ስር 2ኛ ከሳሽ) እናት ሙሉ ሮቢ እና የስር 3ኛ ከሳሽ እናት ዘውዲቱ ሮቢ ናቸው፡፡ የአያታችን ልጆች አራቱም በህይወት ስለሌሉ የአያታችን ወራሾች መሆናችን ተረጋግጦ አከራካሪውን በተጠሪ(ስር 2ኛተከሳሽ) እጅ የሚገኝ በሮቤ ከተማ በአዳ ሮቤ ቀበሌ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት እንዲሁም በክሱ ከተራ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቁጥር 2ኛ-6ኛ ስፋቱና አዋሳኙ የተገለጸው የእርሻ መሬት እንዲሁም በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ ኦንሾ በሚባል አካባቢ የሚገኝ ስፋቱ 16 ጥማድ የሚሆን እና አንድ ሺህ እግር ባህርዛፍ የሚገኝበትን በማለት እንዲሁም ሌሎች የእርሻ መሬት እና መኖሪያ ቤት በመዘርዘር አያታችን ከተከሳሾች ጋር ስትጠቀምበት ቆይታ ለወራሾቹ የሚገባውን እና ስር ከሳሾች በቤተሰባችን ምትክ አያታችንን መውረስ እንድንችል እንዲረጋገጥልን እና ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሀብትና ይዞታ ከመሰረቱ የአያታችን መሆኑ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ስር 1ኛ ተከሳሽ ባቀረቡት መልስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም ባቀረቡት መቃወሚያ በክሱ ተ.ቁ B የተገለጸው ይዞታ ላይ ሟች የከሳሾች አያት ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ በህይወት እያለች ምንም መብት አልነበራትም፡፡ ሟች በህይወት እያለች ይዞታውን ተጠሪ ለ20 አመት በግሌ ይዤ በእጄ ያለ ነው፡፡ ሟች መብት ያላት ቢሆንም እንኳ በህይወት ካለችበት ግዜ አንስቶ ይዞታው ከ15 አመት በላይ በእጄ ስለቆየ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ ስለሆነም ከሳሾች ሟች የሌላትን መብት ሊያነሱ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረቡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ መሰረቱ የአባቴ ሲሆን ሟች በህይወት እያለች ተላልፎልኝ ለሀያ አመት በእጄ አስገብቼ በስሜ ተመዝግቦ የባለቤትነት መታወቂያ ወረቀት ያለኝ በመሆኑ፣ የመንግስትም ግብር እየከፈልኩበት በመሆኑ ሟች በዚህ ይዞታ ላይ መብት ስለሌላት ከሳሾችም ሟች የሌላትን መብት ለመውረስ መብት ስለሌላቸው ይህ ይዞታ የተጠሪ የግል ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በሮቤ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት መሰረቱ የኡርጎ ጂማ መሆኑ እውነት ነው፣ ሆኖም ቤቱን ሟች በህይወት እያለች በ13/4/04ዓ.ም በተደረገ የሽያጭና ግዢ ውል ሸጣልኝ ማስረጃ ተሰጥቶኝ በእጄ ያለ እና አሮጌውን ቤት አፍርሼ ዘመናዊ በሆነ መልኩ በራሴ ወጪ ያለማንም ተቃውሞ በላዩ ላይ የሰራሁበትና ከ2004ዓ.ም ጀምሮ በእጄ ያለ በመሆኑ ይህ የመኖሪያ ቤት አመልካችን ጨምሮ ለስር ከሳሾች በውርስ የሚተላለፍ ንብረት አይደለም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አሁን የሰበር ክርክሩ ላይ የሌሉ የስር ጣልቃገብም የራሳቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ፍርድቤቱም ግራቀኙን በቃል ካከራከረ፣ ለጉዳዩ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ጭብጦች ከያዘ እና የስር ከሳሾችን፣ ተከሳሾችን እና ጣልቃገብ ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ፍሬጉዳዩን በተመለከተ ጉዳዩን መርምሮ የተሰሙት ምስክሮች ቃል ሲመዘን ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ያቀረባቸው ምስክሮች በክርከሩ ውስጥ የተገለጹት ይዞታዎች የተጠሪ መሆናቸውን እና አመልካችን ጨምሮ የስር ከሳሾች አያት በዚህ ይዞታ ላይ መብት የሌላት መሆኑን፣ ይዞታው ለአስራ አምስት አመት በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) እጅ መቆየቱን አላረጋገጡም፡፡ አመልካችን ጨምሮ ስር ከሳሾች እና የጣልቃገብ ምስክሮች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ ከመሰረቱ የስር ከሳሾች አያት የወ/ሮ ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑን እና እሳቸው ከሞቱ በሃላ ይዞታው ተጠሪን ጨምሮ በስር ተከሳሾች እጅ መግባቱን የመሰከሩ በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የሟች የወ/ሮ ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በሮቤ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤትን በተመለከተ ተጠሪ በ13/4/04ዓ.ም በተደረገ የግዢና ሽያጭ ውል ያገኘ ስለመሆኑ ላቀረበው ክርክር በ13/4/04ዓ.ም በተጻፈ የሽያጭና ግዢ ውል መግዛቱን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) በ13/4/04ዓ.ም በተጻፈ የግዢና ሽያጭ ውል ቀደም ብሎ በ27/3/04ዓ.ም የስም መቀየሪያ ብሎ ክፍያ መፈጸሙን የሚገልጽ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የግዢና ሽያጭ ውሉ ሳይፈጸም በቅድሚያ የስም ቅያሪ ክፍያ የሚፈጸምበት አግባብ የለም፡፡ በሌላ በኩል ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ በ9/2/04ዓ.ም በፈጸሙት የውክልና ውል ይህን ንብረት እንዲሸጥ፣ ስም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲቀይር፣ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ እንዲችል ሃይሌ ሮቢ ለሚባል ሰው ውክልና የሰጠች መሆኑን የቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ ያስረዳል፡፡ ሆኖም ይህን የመኖሪያ ቤት ሌላ አካል እያስተዳደረው ባለበት ቦታ ሟቿ ለዚህ አካል የሰጠችውን ውክልና ሳታነሳ ንብረቱን የምትቆጣጠርበት መንገድ የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ሟች ኡርጎ ጂማ ከተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ጋር ያደረገችው የመኖሪያ ቤቱ የሽያጭና ግግር ውል ተቀባይነት ያለው ስላልሆነ ተጠሪ የመኖሪያ ቤቱን በሽያጭና ግግር ውል አፍርቼዋለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር ውድቅ ሆኗል፡፡ ስለሆነም በክሱ ውስጥ የተገለጸው የእርሻ መሬት ይዞታ የሟች ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑን እና ለክርክሩ መነሻ በሆነው መኖሪያ ቤት የተደረገው የሽያጭና ግግር ውል ውድቅ ተደርጎ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ እና በክሱ ውስጥ የተጠቀሰው የመኖሪያ ቤት የአመልካች እና ሌሎች ስር ተከሳሾች አያት ሀብትና ንብረት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በውሳኔው ላይ በተገለጸው መልኩ ክፍፍል እንዲፈጸም ወስኗል፡፡

ተጠሪ ከላይ በተገለጸው በተጠሪ እጅ ይገኛል በተባለው የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ እንዲሁም በሮቤ ከተማ በኦዳ ሮቤ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም የስር ከሳሾችን እና ስር ጣልቃገብን መልስ ከተቀበለ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) እጅ ይገኛል የተባለው በክሱ ውስጥ አዋሳኙ እና ስፋቱ ተገልጾ የቀረበውን ይዞታ በተመለከተ ተጠሪ ሟች በህይወት እያለች በእጁ በማስገባት ሁለት ዙር በስሙ አስመዝግቦ በሱ ስም ተፈጽሞ ሲጠቀምበት የነበረ ስለመሆኑ ከሰው እና ከጽሁፍ ማስረጃ ላይ የምንገነዘበው በመሆኑ በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማሻሻል በተጠሪ እጅ ይገኛል የተባለው አዋሳኞቹ እና ስፋቱ በክሱ የተገለጸው የመሬት ይዞታ መሰረቱ የሟችቷ ቢሆንም ሟች በህይወት እያለች ተጠሪ(ስር 2ኛ ተከሳሽ) ሲጠቀምበት የቆየ ስለሆነ የግል ይዞታው በመሆኑ ከውርስ ውስጥ እንዲወጣ በማለት ወስኗል፡፡

በሮቤ ከተማ የሚገኘው አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሱትን ስፋቱ 620ካ.ሜ የሆነ ባለ 150 ቆርቆሮ ቤት ያለበት ቦታ በ13/4/04ዓ.ም በሟች እና በተጠሪ መካከል በተደረገ የሽያጭ ውል ለተጠሪ ተላልፎ ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ በተጠሪ ስም ተቀይሮ እሱም የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ወረቀት ተሰጥቶት ያለው መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ የግል ንብረቱ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የስር ከሳሾች እና ስር ጣልቃገብ ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ በዚሁ ላይ የስር ከሳሾች እና ስር ጣልቃገብ የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሳኔ አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት አይቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ከስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ያሉት ፍ/ቤቶች በተጠሪ እጅ የሚገኘው የመሬት ይዞታ እና በሮቤ ከተማ የሚገኘው በክሱ የተጠቀሰው መኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲሻር እና የስር የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸና፣ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው በተጠሪ እጅ የሚገኘው የእርሻ መሬት የአመልካች አውራሽ ወ/ሮ ኡርጎ ጂማ ይዞታ መሆኑ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ በተመለከተበት ሁኔታ ለተጠሪ እንዲሆን የተወሰነበትን እና በሮቤ ከተማ ኦዳ ሮቤ ቀበሌ ውስጥ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሚገኘውን 620ካ.ሜ ይዞታ ለተጠሪ ተሸጧል የተጠሪ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ24/12/13ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ በ15/2/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ ከስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ያሉት የበላይ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፣ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በ6/3/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የሰጡት ትእዛዝ እና ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የስር የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በህግ በተሰጠው ማስረጃዎችን የመመርመር እና የመመዘን ስልጣኑ በስር የሲናና ወረዳ ፍ/ቤት የተሰሙትን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ እና መዝኖ በተጠሪ እጅ ይገኛል ተብሎ በክሱ አዋሳኙ እና ስፋቱ የተገለጸው የእርሻ መሬት ይዞታ የተጠሪ የግል ይዞታ ነው ስለሆነም ከውርሱ እንዲወጣ በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በሮቤ ከተማ በኦዳ ሮቤ ቀበሌ የሚገኘው አዋሳኞቹ በክሱ የተገለጹትን ስፋቱ 620ካ.ሜ የሆነ ባለ 150 ቆርቆሮ የመኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ፣ በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲሁም በዚሁ ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰበር ሰሚ ችሎት አይቀርብም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(1) እና የኢ.ፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) ከደነገጉት አንጻር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የባሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 31939 በ9/7/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 32664 በ20/8/13ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 375407 በ25/9/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

4. በዚህ መዝገብ በሰበር አጣሪ ችሎቱ በ24/12/13ዓ.ም ለክርክር ምክንያት የሆነው በሮቤ ከተማ ኦዳ ሮቤ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘው 620ካ.ሜ የከተማ ይዞታ እና ንብረት እንዳይሸጥ ለሌላ 3ኛ ወገን በማናቸውም ሁኔታ እንዳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሮቤ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ኤጀንሲ ይጻፍ፡፡

5. ውሳኔው በ2/9/14ዓ.ም ተነቧል፡፡

6. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም